# ሩጫው ተጧጡፏል። መዳረሻው የት ነው? እስኪ ለጠይቃችሁ!

*አንዱዓለም ተፈራ፤ ሐሙስ፣ የካቲት ፳፪ ቀን፣ ፳፻፲ ዓመተ ምህረት ( 3/1/2018 )*

የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ በትኩረት ለምንከታተለው ሁሉ፤ ባሁኑ ሰዓት ከመካከላችን ባሉ አንዳንድ ድርጅቶችና በውጪ ኃይላት በኩል፤ የነገዋን ኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ለመወሰን፤ የትንቅንቅ ሩጫው ተጧጡፏል። ወደድንም ጠላንም ይህ ወሳኝ የሆነ ጥድፊያ፤ እያንዳንዳችን ላለንበትና ለምንኖርበት የነገ ሁኔታ፤ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው። እናም ትኩረታችን ከመቼውም የበለጠ ሊሰበው የሚገባ ጉዳይ ነው። ምንድን ነው? ምን ያህል እያንዳንዳችንን ይነካናል? ይህ ነው የዚህ ጽሑፍ ትኩረት።

በተጨባጭ ያለው የሀገራችን የፖለቲካ ሂደት፤ ባጭሩ ቢገለጥ፤ በየቦታው የተበታተነ ነው። በማዕከል ከተቀመጠው የትግሬዎች መንግሥት ጀምሮ፤ ማዕከልነት እስከሌለው የታጋዩ ክፍል ድረስ፤ አጥናፉን የሞሉ ነጠብጣቦችና የጓጎሉ ጠጣሮች የፖለቲካ ጀምበሩን ሞልተውታል። አጀንዳቸውም እንደመልካቸው የተለያየ ነው። በዚያው ልክ ደግሞ፤ ከአሜሪካ እስከ ቻይና፤ ከአረብ ሀገሮች እስከ አውሮፓዊያን ድረስ፤ መዘንጠያ ቢላዎቻቸውን እና ማፈሻ አካፋዎቻቸውን ይዘው አሰፍስፈዋል። ሕዝቡ በምንም መንገድ ሊሳተፍ እንደማይችል ብረዳም፤ አብዛኛው ታጋይ ክፍል የማያውቀው ሂደት አደገኛ እንደሆነ እረዳለሁ። ይህ በምን የሚደመደም ነው? ትንቢት ለመናገር ቃጥቶኝ ሳይሆን፤ ፍርሃቴን ላጋራችሁ ነው።

እስኪ አሁን በዚህ ሰዓት እየተደረጉ ባሉ ሂደቶች ላይ እናተኩር። በታጋይ ድርጅቶች መካከል የተለያዩ ስብሰባዎች እየተደረጉ ነው። ይበል የሚያሰኝ ነው። ነገር ግን፤ አመርቂ የሆነ ውጤታቸውን ለማየት አልበቃንም። ለንደን ላይ ሆነ ዋሺንግተን ዲ. ሲ. በተደጋጋሚ እየተደረጉ ያሉ የታጋይ ድርጅቶችና የውጪ ሀገር ኃይሎች ግንኙነቶች አሉ። እነኚህ ደግሞ፤ በዝግ አዳራሽ ከመደረጋቸው በላይ፤ ማን ተሳትፎ ማን እንደቀረ፤ ማን ተጋብዞ ማን አልቀበልም እንዳለ የምናውቀው ጉዳይ የለም። እኔ አላውቅም ማለቱ ይሻለኛል። ይሄ ሁሉ ሽርጉድ ሁለት ነገሮችን አሳስቦኛል።

የመጀመሪያው የነገው የሀገራችን ጉዳይ፤ በዚህ መንገድ ከተከናወነ፤ እምቡዋለሌ ትግሉ መቀጠሉ ነው። ይህ ሽርጉድ፤ ኢትዮጵያን ወይንም ኢትዮጵያዊያንን ማዕከል ያደረገ አይደለም። እናም ተጠቃሚና ተጎጂ ያለበት ሂደት ነው። ታዲያ የተጎዳው አንገቱን ደፍቶ ይቀመጣል ባዩ ማነው ! ! !

ሁለተኛው፤ የትግሉም ሆነ የውጤቱ ባለቤት ታጋዩና ሕዝቡ መሆኑ ቀርቶ፤ የፖለቲካ ቅመራውን የተካኑት የሚያሽከረክሩት መሆኑ ነው። ይህ ሁሉ ወደ ሁለት ትውልድ በመሸጋገር ላይ ያለ ታጋይ የከፈለው መስዋዕትነት ከንቱ ሲገባ፣ ዝም ብለን እያየን ነው! እውነት ነገ፤ በዚህ መንገድ ተኪዶ፤ ሰላምና ብልጽግና በኢትዮጵያ ይሰፍናል ብለን እናምናለን ! ! !

ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ እኛ ነን። ኢትዮጵያዊያን ነን። በተለይም በትግሉ መድረክ ላይ የምንገኘው ነን። የኛ በተወሰነም መታገያ ጉዳይ ተሰባስበን አለመገኘታችን፤ ለብልጣ ብልጦችና የውጪ አነኳሪዎች ቦታውን በው አድርጎ ከፍቶ ሠጣቸው። የትግሉ ማዕከል የት ነው? አዲስ አበባ? ዋሺንግተን ዲ. ሲ.? ለንደን? ትግሉ በማን ዙርያ ይሽከረከራል? በትግሬዎቹ መንግሥት? በታጋይ የዐማራና የኦሮሞ ወጣቶች? በኦፒዲኦና በብአዴን? በሰላማዊ ታጋዮችና በትጥቅ ትግል በሚያምኑ ታጋዮች? በሳይቨር ታዳሚዎችና የዕለቱ ወሬ ምን እንደሆነ አሳዳጆች? በምን አጀንዳ ይቃኛል? በሀገር አቀፍ የትግል ዕሴቶች? በብሔር ነፃ አውጪዎች ምኞት? ዘሩ እንዲጠፋ በተዘመተበት? የወርቅ ዘር ነንና ያፈተተንን እናድርግ አትንኩን ባዮች? በዛ የዓለም ክፍል ጉዳይ አለኝና፤ የፈለግኩትን መንግሥት ላቋቁም ባይ የውጪ መንግሥት? አጀንዳው ምንድን ነው?